# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

*ተዛማጅ ሠነዶች፡-* JEA, JEA-RC, JEA-RD, JEA-RE, JEB-RA, JEE-RA, JOA-RA
*ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-* የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ቢሮ

## ስለ ተማሪዎች ምዝገባ

**I. ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JEA ድንጋጌ መሠረት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ነዋሪ የሆነ(ች) እና ነዋሪ ያልሆነ(ች) ተማሪ ምን ማለት እንደሆነ ለመወሰን መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ መኖሪያ፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና የት/ቤት ምዝገባ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎችን ለመመዝገብ ትክክለኛ የመኖሪያ ቦታን እና ሌሎች መመዘኛዎችን የመወሰን ሂደቶችን ለመደንገግ

**II. ትርጓሜ**

A. እውነተኛ የመኖርያ ቦታ ማለት በቅን ልቦና የተገለፀ የአንድ ሰው ትክክለኛ መኖሪያ ቦታ ማለት ሲሆን፣ ጊዜያዊ መኖሪያን ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነጻ ትምህርት ዕድል ለማግኘት የተደረገ የይምሰል መኖሪያን አያካትትም። ይሁን እንጂ፣ አሁን ባለው የመኖሪያ ቦታ በዘላቂነት ወይም በቋሚነት መኖር የግድ አስፈላጊ አይደለም። እውነተኛና ያልተጭበረበረ የተማሪ መኖሪያ ትክክለኛነቱ በግለሰብ ደረጃ መታየት አለበት። ማስረጃ ካልቀረበ፣ የወላጅ/የሞግዚት መኖርያ በአንፃሩ እውነተኛ የነዋሪነት ማረጋገጫ ነው።

የተማሪው(ዋ) ወላጆች/ሞግዚቶች ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነና የተማሪው(ዋ) ትክክለኛ የመኖሪያ ማስረጃ የማይገኝ ከሆነ፣ ብቸኛው አማራጭ የልጅ አሳዳጊነት መብት የተሰጠው/የተሰጣት ወላጅ/ሞግዚት ወይም ልጁ/ልጅቱ ዘወትር የሚኖርበት/የምትኖርበት ሥፍራ ህጋዊ መኖርያ ተብሎ ይወሰዳል። የተማሪን መደበኛ መኖሪያ ለመወሰን አጠቃላይ ሁኔታዎችን ያገናዘበና በመረጃ-የተደገፈ መሆን አለበት። ሠራተኞች በተለይም በትምህርት ቀናት ተማሪው(ዋ) የት እንደሚኖር/እንደምትኖር የተንከባካቢነት/የሞግዚትነት ትእዛዝ ወይም ስምምነትን ጭምር ይመለከታሉ።

ብቁ ለሆነ(ች) ተማሪ እውነተኛ የመኖርያ አድራሻ ሚሆነው ከወላጅ/ከአሳዳጊ ተለይቶ የሚኖር ነው።

B. አሜሪካዊ ዜጋም ቢሆን ዜግነት የሌለውም ቢሆን፣ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ፣በወቅቱ የትምህርት አመት የመጀመሪያ ቀን በሴፕቴምበር 1 ቢያንስ 5 አመት የሞላው እና ከ 20 አመት እድሜ ያልበለጠ(ች)፣ ማለት ነው።

C. ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ፣ አሜሪካዊ ዜጋ ቢሆንም/ባይሆንም ወይም ዜግነት የሌለውም ቢሆን/የሌላትም ብትሆን፣ ለአካለ መጠን የደረሰ(ች) (ማለትም 18 አመት እድሜ) ወይም ከ18 ዓመት እድሜ በፊት ከወላጅ ቁጥጥር ነፃ የወጣ(ች)፣ ነገር ግን በወቅቱ የትምህርት አመት ት/ቤት የመጀመሪያ ቀን ላይ ከ 20 ዓመት እድሜ ያልበለጠ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

D. በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሠረት፣ የአካባቢ ትምህርት ቤት ማለት፣ተማሪው(ዋ) በሚኖርበት/በምትኖርበት አካባቢ የተቋቋመ ት/ቤት ወይም በተማሪ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መሠረት የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ማለት ነው።የአካባቢ ትምህርት ቤት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ከዚህ ዝርዝር ላይ MCPS Division of Capital Planning Office፦ (montgomeryschoolsmd.org/departments/planning) መረጃ ማግኘት ይቻላል።

## III. ዳራ

ከሚከተሉት በስተቀር ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ እውነተኛ ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎችን ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን (ወይም ሰክሽን IV.B. ላይ እንደተገለጸው ብቁ ተማሪዎችን) ሁሉ ለምዝገባ መቀበል አለባቸው።

A. አንድ ተማሪ በወቅቱ ከሌላ ትምህርት ቤት የታገደ(ች) ወይም የተባረረ(ች) ከሆነ፣ MCPS የሌላውን ትምህርት ቤት ሃሳብ ወስዶ ተገቢውን ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፣ ይህም የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል፡ MCPS የታገደ(ች)ውን ወይም የተባረረ(ች)ውን ተማሪ ምዝገባ ሊያዘገይ ወይም በአጠቃላይ በትምህርት ቤት ፕሮግራም እንዳይመዘገብ/እንዳትመዘገብ ሊከለክል ይችላል።

B. የተማሪው(ዋ) አለመባረር ከሪኮርድ እስከሚረጋገጥ ድረስ የተማሪው(ዋ) ምዝገባ ጊዜያዊ እንደሆነ ይቆጠራል።

## IV. የተማሪዎች ምዝገባ ስርአት

A. ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ በመደበኛነት ነዋሪዎች መሆናቸውን ያሟሉ ተማሪዎች በሙሉ፣ ከዚህ በታች ሰክሽንስ IV.A.1. እና IV.A.2 ከተገለጸው ሁኔታ በስተቀር በየአካባቢያቸው ትምህርት ቤቶች ይመዘገባሉ/ይገባሉ።

1. የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የመኖሪያ አድራሻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ኮንሶርቲየም ኮሙኒቲ MCPS Consortia ቢሮ መመዝገብ እና በት/ቤት ምርጫ ሂደት መግባት እና ትምህርት ቤት መመደብ አለባቸው። የምርጫ ሂደት መረጃ ከኮንሶርሺያ ምርጫ እና መተግበሪያ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል (montgomeryschoolsmd.org/departments/school choice) ማግኘት ይቻላል።

2. በሴፕቴምበር 1 እድሜያቸው 7 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በዩናይትድ ስቴትስ ወይም በዩኤስ የትምህርት ስርዓት (ማለትም የመከላከያ ትምህርት ቤቶች ወይም በውጭ አገር ውስጥ የሚገኝ እውቅና ያለው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤት) ትምህርት ቤት ያልተማሩ ተማሪዎች ወደ አለምአቀፍ የት/ቤት ምዝገባ እና ምደባ (IAE) ክፍል ቀርበው መመዝገብ አለባቸው። የእነዚህ ተማሪዎች ምዝገባ የሚከናወነው "MCPS Regulation JEA-RC" መሠረት ይሆናል፦ዓለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ/Enrollment and Placement of International and Foreign Students

3. ከአካባቢያቸው ምድብ ትምህርት ቤት ወደሌላ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎችን በሙሉ ርእሰምምህር/ተወካይ ወደየራሳቸው የአካባቢ ምድብ ት/ቤት መመለስ ይኖርበ(ባ)ታል።አግባብነት ያለው ከሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ "MCPS Regulation JEE-RA"፣"የተማሪ ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች" ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ስለ ትምህርት ቤት ምደባ የመቀየር ሒደት መረጃ መስጠት ይቻላል።

B. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ትክክለኛ ነዋሪነት ያላቸው ብቁ ተማሪዎች በሙሉ ከላይ በሰክሽን IV.A እንደተገለጸው በመኖሪያ አካባቢያቸው ትምህርት ቤቶች ይመዘገባሉ።

C. በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመዝገብ የሚኖርባቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ሁኔታዎች የሚያካትቱት–

1. ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ በተቋቋመው የትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ (ከመመዝገቢያው ቀን ጀምሮ 60 ቀናት ውስጥ የሚጠናቀቅ ቤት ለመግዛት የተረጋገጠ ውል) ወይም በሚመዘገብበት ት/ቤት አካባቢ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 60 ቀናት ውስጥ የሚጀምርና ወደፊት የሚቆይ የቤት ኪራይ ውል መቅረብ አለበት፤ ወይም

2. MCPS ደንብ JEA-RD መሠረት ብቃት ያለው/ያላት የቤት አልባ ተማሪ ወይም ብቻው(ዋ)ን የሚኖር ቤት አልባ ወጣት ተማሪ ምዝገባ፣ ወይም

3. ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ በሜሪላንድ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ አማካይነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ በቡድን መኖሪያ ቤት፣በህፃናት ልጆች ማሳደጊያ፣ በይፋ የሚታወቅ ዝምድና ላላቸው እንክብካቤ እንዲያደርጉ ይመደባል/ትመደባለች። እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች፣ MCPS ቅፅ 560-35፣በሜሪላንድ ስቴት ክትትል የሚደረግበት የልጅ እንክብካቤ እና የትምህርት ሪኮርዶች ዝውውር፣ መሞላት አለበት፤ ወይም

4. በሜሪላንድ ተቀባይነት ባለው በህጋዊነት ይፋ ያልሆነ ዘመድ በመጠጋት ነዋሪ የሆነ(ች) ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ፡-

   a) ቤተሰብ ከባድ ችግር ላይ በመውደቁ ምክንያት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ከልጁ/ከልጅቱ ጋር በጋብቻ ወይም በደም ዝምድና /fifth degree of consanguinity፣ ወደ ሚገናኙት ዘመድ በጥገኝነት ከመምጣቱ(ቷ) በፊት በሜሪላንድ ነዋሪ የሆነ(ች) ተማሪ ላይ የሜሪላንድ ይፋዊ ያልሆነ የዝምድና እንክብካቤ ተግባራዊ ይሆናል።

   b) ተማሪው(ዋ)ን የሚንከባከበው ዘመድ MCPS ቅጽ 334-17 ይፋዊ ያልሆነ የዝምድና እንክብካቤ ለሚደረግላቸው ልጆች በጽሑፍ የቀረበ ቃለ መሃላ/AFFIDAVIT: Children in Informal Kinship Care መፈረም አለበት፣ ከልጁ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት ይፋዊ ያልሆነ የዝምድና እንክብካቤ እየተደረገ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

   c) በሜሪላንድ ይፋዊ ያልሆነ በዘመድ ጥገኝነት ከባድ የቤተሰብ ችግሮች ተብለው የተገለጹት፡-

      (1) የህልፈተ ህይወት ሠርተፊኬት ወይም በሌላ ሠነድ/ዶኩመንት የተረጋገጠ የወላጅ/የሞግዚት መሞት፣

      (2) በሃኪም መረጃ የተረጋገጠ የወላጅ/የሞግዚት በጣም መታመም፣የሃኪም ማስረጃ፣ ማስታወሻ፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ ቅጂ/ኮፒ፣

      (3) በህክምና ባለሙያ የተገለጸ ወይም ከወላጅ/አሳዳጊ በተጻፈ ደብዳቤ የተረጋገጠ የወላጅ/የአሳዳጊ የዕፅ ሱሰኝነት፤

      (4) የወላጅ/ሞግዚት እስራት፣ በህጋዊ ተቋም ሠነድ/ዶኩመንት፣ ከእስር ቤት፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ የተደገፈ ከሆነ፣

(5) የወላጅ/ሞግዚት ለወታደራዊ ግዳጅ የተመደቡ ከሆነ፣ በወታደራዊ ተቋም ወይም በሌላ ሠነድ ከተረጋገጠ፣ ወይም

(6) በወታደራዊ ትእዛዝ ወይም ሌላ ማስረጃ እንደተመዘገበው የወላጅ/የአሳዳጊ ለወታደራዊ ግዳጅ መመደብ፣ ወይም

D. እድሜው(ዋ) ከ18 ዓመት በታች የሆነ ብቁ ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ በፍርድ ቤት ከተሰየመ(ች) አሳዳጊ ወይም ሌላ ጎልማሳ ጋር ሁኔታው ለመደበኛ ዝምድና እንክብካቤ የማይመች ከሆነ እና ወላጆች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ትክክለኛ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ሆኖ ለመመዝገብ ከፈለጉ የትምህርት ክፍያን ማቋረጥ አስፈላጊ መሆኑን ለማረጋገጥ MCPS ደንብ JEA-RE በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሰረተ ምዝገባ ላይ እንደተገለጸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች IAE ጋር መነጋገር አለባቸው።

E. አንድ ርእሰ መምህር/ተወካይ ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት በቀጥታ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሟላቱን እርግጠኛ ካልሆነ(ች)፣ ርእሰ መምህሩ/ተወያዩ IAE ማማከር እና አስፈላጊ ሲሆን፣ ተማሪው(ዋ)ን ወደ IAE መላክ አለባቸው።

F. ተማሪው(ዋ) የመመዝገቢያ መስፈርቶችን ማማሏቱ/ቷ ከተረጋገጠ፣ ርእሰመምህር/ተወካይ የሚከተሉትን የማስፈጸም ሃላፊነት አለበ(ባ)ት፦

1. የምዝገባ ሂደት ማጠናቀቅ። በምዝገባ ቀጠሮ ቀን ተመዝጋቢው(ዋ) ተማሪ መገኘት አለበ(ባ)ት፣ ተከታዩ ካልሆነ በስተቀር —

   a) በርእሰመምህር(ት)/ተወካይ የተማሪው(ዋ) መገኘት ጉዳይ ተሠርዞ ከሆነ፣ ወይም

   b) በወቅቱ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገበ(ች) እና በ MCPS ክልል ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የሚዛወር/የምትዛወር ከሆነ።

2. MCPS ደንብ JOA-RA "የተማሪ ሪኮርዶች" መሰረት ተገቢውን የተማሪ ሪኮርዶች ማቋቋም።

3. MCPS ደንብ JEB-RA፣ የተማሪዎች ምደባ፣ ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወር፣ የተፋጠነ ትምህርት ምደባ እና በሚገኝበት ደረጃ መቆየት እና JEA-RC፣ በአለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ መሰረት የተማሪ የክፍል ደረጃ እና የትምህርት ክፍል ምደባ።

## V. ለምዝገባ አስፈላጊ ሠነዶች

A. በቦርድ ፖሊሲ ACA መሠረት፥ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ፣ እና የባህል ብቃት፣ MCPS በዜግነት ላይ የተመሰረተ አድልዎ አያደርግም፤ የዜግነት ሁኔታን የሚመለከት መረጃ ይፋ ማድረግ/መሰብሰብ አያስፈልገውም።

B. ትክክለኛ የመኖሪያ ሥፍራ የሚያመለክቱ ማስረጃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት በወላጅ/በአሳዳጊ ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ላይ ነው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ማስረጃዎች የነዋሪነት ቦታን ያመለክታሉ፣ ይሁን እንጂ፣ MCPS ተቃራኒ የሆኑ ማስረጃዎችን ካገኘ፣ ይህ ውሳኔ ሊነሳ (ሊቀለበስ) ይችላል። ከግለሰብ ማረጋገጫ በተጨማሪ፣ MCPS በክፍል-ደረጃ ወይም ትም/ቤት አቀፍ የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ የማጣራት መብት አለው።

C. በወቅቱ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በመማር ላይ ያለ(ች) ተማሪ ቤተሰብ ወደ ሌላ የ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ የተዛወሩ ከሆነ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች አዲስ ለተዛወሩበት አካባቢ ትምህርት ቤት ነዋሪ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

D. ተማሪን MCPS ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ለመመዝገብ ወይም ከ MCPS ከወጡ በኋላ እንደገና ለመመዝገብ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የሚከተለው ኃላፊነት አለባቸው፦

1. MCPS ቅጽ 560-24 ስለ አዲስ ተማሪ መረጃ፣ እና MCPS ቅጽ 565-1 የተማሪ የአደጋ ጊዜ ተጠሪ መረጃ መስጠት፣

2. MCPS ደንብ JEA-RD ላይ ባለው ዝርዝር መሠረት ተማሪው(ዋ) መስፈርቱን አሟልቶ(ታ) ካልሆነ በቀር፣የቤት አልባ ተማሪ ሙብቶች፡የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ፣

a) የተማሪው(ዋ) ስም እና የተወለደ(ች)በት ቀን ማረጋገጫ (ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች የልደት ምስክር ወረቀት፣ ፓስፖርት/ቪዛ፣ የሀኪም ምስክር ወረቀት፣ የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ምስክር ወረቀት፣ የሆስፒታል ምስክር ወረቀት፣ የወላጅ የሠነድ ማረጋገጫ ያለበት የጽሑፍ ማስረጃ፣ የልደት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣ ወይም ሌላ ህጋዊ ወይም የተረጋገጠ መታወቂያ ናቸው)።

b) ፎቶግራፍ ያለበት የወላጅ/የአሳዳጊ ማንነት ማረጋገጫ (ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች፥ የመንጃ ፍቃድ፣ፓስፖርት፣ከሞተር ተሽከርካሪ አስተዳደር የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ወይም ሌላ ህጋዊ የመታወቂያ አይነት)፣

c) ወላጅ/አሳዳጊ ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለው ግንኙነት ወይም የአሳዳጊነት ማረጋገጫ (ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች፥ ወላጆች መሆናቸውን የሚገልፅ የልደት ምስክር ወረቀት፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ የመለያየት ስምምነት ወይም የጋብቻ ፍቺ ውሳኔ ወይም ሌላ ህጋዊ መታወቂያ)፣

d) የክትባት ማረጋገጫ. ተቀባይነት የሚኖራቸው ሰነዶች

(1) የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት (MDH) ቅፅ 896፣ የሜሪላንድ የጤና መምሪያ የክትባት ሰርተፍኬት፣ወይም በሃኪም ወይም በጤና ክሊኒክ በኮምፒውተር የተሞላ ቅጽ፣ እና

(2) ወላጆች/ሞግዚቶች በኃይማኖታዊ እምነታቸው ምክንያት ክትባት(ቶች) የማይፈልጉ ከሆነ ቅጽ/MDH Form 896 ተገቢ ሠነድ ይሆናል

e) የነዋሪነት ማስረጃ

(1) የቤት ባለቤት (ተቀባይነት ያለው ሰነድ የአሁን የንብረት ታክስ የተሠራበት ሠነድ ነው)

(2) ተከራይ

(a) ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የኪራይ/የሊዝ ሠነድ ነው።

(b) የመጀመሪያው የኪራይ/ሊዝ ሠነድ ወቅቱ ያለፈበት ከሆነ፣ ወቅታዊ የዩቲሊቲ ክፍያ ሠነድ (የመብራት፣ የውኃ፣ የጋዝ) ወይም የኪራይ/ሊዝ የተራዘመበት ሠነድ መቅረብ አለበት።

(3) የጋራ/የደባልነት ቤት

ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት በሚገኝበት አካባቢ በህጋዊነት ከሚኖሩ የቤት ባለቤት ወይም ከተከራይ ጋር ተጋርተው በደባልነት እየኖሩ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ከፈለጉ ቅጽ - MCPS Form 335-74፣ የቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosure፣ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው።

(a) MCPS ቅጽ 335-74 ከላይ ሰክሽን V.D.2.e) (1)(2) ላይ እንደተገለጸው ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ የሚኖርበትን የቤት ባለቤት ወይም ተከራይ የመኖሪያ ማረጋገጫ እንዲሰጡ ያስፈልጋል፣ እና

(b) ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ቤት ለመከታተል ብቻ ሳይሆን መደበኛ መኖሪያቸው ከእነርሱ ጋር መሆኑን በማረጋገጥ የቃለመኃላ ቅጽ "MCPS Form 335-74" ሞልተውና ፈርመውበት ኖቶራይዝ ተደርጎ (የሠነድ ማረጋገጫ) መቅረብ አለበት፣ እና

(c) ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ በዚህ አድራሻ ነዋሪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ሦስት ሠነዶች ማቅረብ አለባቸው። (እነዚህ ሠነዶች ለምሳሌ፡- MCPS “Student Record Keeper Manual"፣"MCPS Form 560-24B""Quick Guide to Enrollment" ውስጥ ተካተዋል። ተሞልቶ የተፈረመበት እና ኖተራይዝድ (የሠነድ ማረጋገጫ) ያለው MCPS ቅጽ 335-74 ከሦስቱ የአድራሻ ማረጋገጫዎች እንደ አንዱ ሊቆጠር ይችላል።)

(4) በትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በተማሪ ሰራተኛ የቤት ጉብኝት፣ MCPS ቅጽ 560-34፣ አስፈላጊ ሰነዶችን ማቅረብ ባይችሉምበቤት ጉብኝት የተረጋገጠ የነዋሪነት ሰነድ በመጠቀም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች ባሉበት ሁኔታ የመኖሪያ ቦታን ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

## VI. የምዝገባ ይግባኝ ሂደት

A. ተማሪው(ዋ) የመኖሪያ ቦታ ማረጋገጫን በሚመለከት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የማያሟላ መሆኑን በመወሰን የተመዘገበ(ች)ውን ተማሪ ርእሰ መምህሩ(ሯ) ካስወጣ(ች)፣MCPS ደንብ KLA-RA ላይ በተገለጸው መሠረት ሲጋቶች፣ቅሬታዎች እና ለት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ይግባኝ ማቅረብ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ 15 ቀናት ውስጥ በቀጥታ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ለተወካዩ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ሰክሽን IV.D. ድንጋጌ መሠረት ለት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ በሚሉበት ጊዜ ተማሪው(ዋ) በተመደበበት ትምህርት ቤት እየተማረ(ች) መቆየት አለበ(ባ)ት።

B. ሰክሽን IV.C-E ላይ እንደተገለጸው IAE እንደ ትክክለኛ ነዋሪ ለመመዝገብ የሚከለክል የምዝገባ ውሳኔ ከሰጠ፤ MCPS ደንብ KLA-RA፣ ስጋቶች፣ ቅሬታዎች እና ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማቅረብ፣ሰክሽን IV.D ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ 15 ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

C. በይግባኝ ሂደት ወቅት፣ተማሪው(ዋ) ት/ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ነዋሪ ያልሆነ ተማሪ እንደሚከፍለው የትምህርት ክፍያ ከዓመት ክፍያ 10 በመቶውን የመክፈል ግዴታ አለበ(ባ)ት። MCPS ቅጽ 335-73A፣ ነዋሪ ያልሆነ የትምህርት ክፍያ የሚከፍል ተማሪ የምዝገባ ጥያቄ፣ ቅጽ መሞላት አለበት። የመጀመሪያው ውሳኔ ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ የትምህርት ክፍያው/Tuition በሙሉ ወይም በከፊል ተመላሽ ይደረጋል።

**IAE ዳይሬክተር ውሳኔ እና MCPS ደንብ JEA-RE ላይ እንደተገለጸው በክፍያ ላይ የተመሰረተ ምዝገባ ክፍያው እንዲቀር ሊፈቀድ ይችላል።**

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-301, §7-305, and §7-403; Code of Maryland Regulations, §13A.02.06.02, Definitions, §13A.02.06.03, State Financial Assistance under the Foundation Program, §10.06.04.03, Required immunizations, §10.06.04.05, Religious exemptions; MCPS Student Record Keeper Manual.

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡- ቀደም** ሲል ደንብ 355-3 እና JEB-RA አካል የነበረ ሲሆን፣ ኦገስት 26,1987 እንደ አዲስ ደንብ ሆኖ ተመሠረተ፥ ሜይ 2,1995 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 4, 1996 ተሻሽሏል፣ ጁን 27, 1997 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 6, 2001 ተሻሽሏል፣ ማርች 10, 2005 ተሻሽሏል፣ ፌብሯሪ 6, 2008 ተዛማጅ ይዘቶች ተጨምረውበት ተሻሽሏል፣ ጁላይ 29, 2015 ተሻሽሏል፣ ሰፕቴምበር 24, 2018 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 10, 2019 ተዛማጅ ይዘቶች ታክለውበት ተሻሽሏል ጁን 5, 2024 ክለሳ ተደርጎበት ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024